## ዲዎጋን

“ሰው እፈልጋለሁ!” እያለ ዲዎጋን
ብርሃኑን አብርቶ አልደበቀው በጋን፣
በቀን ብርሃን ኩራዝ አብርቶ እየዞረ፣
ሰው አጣሁ እያለ ሰውን ሲያደርቅ ኖረ።
ቀለድ እያስመሰለ ሲያወራ፣ ሲያወጋን፣
ሰው አይደላችሁም በማለቱ ወጋን!
“ሰው ማለት፣ ደግሞም ሰው ማለት
ሰው የሚሆን ነው ሰው የጠፋ ዕለት!”

ገ/ኢ. ጉርፉ።



Διογένης